# *አቦ ከዋናው አጀንዳ ባትነቅሉን!!*

*ከሻለቃ ኢድሜሱ 25/11/2009ዓ.ም*

ለዚህ ፅሁፍ መነሻ የሆነኝ በዚሁ ድረ ገፅ ላይ ሌተና ጀነራል ፃድቃን ገብረትንሳኤ *"የአገራዊ ደህንነትና የውጪ ጉዳይ ፖሊሲ ጉዳይ"* በሚል ርእስ ያስነበቡን ፅሁፍ ነው፡፡ ባለንበት ዘመን የደህንነት ጉዳይ ለመንግስት ብቻ የሚተውና መንግስት ብቻውን ይወጣው የሚባል ጉዳይ ሳይሆን እሳቸው እንዳሉት የእያንዳንዱን ዜጋ የእለት ተእለት ኑሮውንም ሆነ ህልውናን የሚመለከትና የሚነካ ጉዳይ በመሆኑ በአገራችን የውጪ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲ ላይ እንደእኔ ያላቸውን ሀሳብ ለመሰንዘር ለሚፈልጉ ዜጎች የበኩላቸውን ለመሰንዘር እንዲችሉ ጀነራሉ በጽሁፋቸው ያላቸውን እነሆ በማለታቸው ሊመሰገኑ ይገባል፡፡

ጀነራሉ የፅሁፋቸውን አላማ በሁለተኛው ገፅ ላይ ሲገልፁ *"......መሰረታዊ በሆነና ሁሉንም ጉዳያችንን በአንድ ወይም በሌላ መልኩ በሚነካ የአገር ደህንነት ጉዳይ ላይ ሀሳብ ለመስጠት ነው፡፡ የፅሁፉ ዋና ይዘት አንዳንድ የፖሊሲ አማራጭ ሀሳቦችን ለመሰንዘር አይደለም::"* ካሉን በኋላ ወረድ ብለው *የአሁኑ ፅሁፍ "ዋና አላማ የፖሊሲ <u>አማራጭ ሀሳቦችን ለመሰንዘር ሳይሆን</u> የአገር ደህንነትና የውጪ ጉዳይ ፖሊሲ ምንነቱንና የሚሰጠውን ጠቀሜታ........ሀሳብ ለማቅረብ ነው፡፡"* ብለውናል፡፡ ነገር ግን ፅሁፋቸውን ከጅምሩ እስከመጨረሻው ሳነብ በዚህ መንደርደሪያ የጀመሩት አላማ በውስጣዊ ይዘቱ ከተነሱበት መንደርደሪያ ያፈነገጠ ሆኖ ስለተሰማኝ ባነሱት ሀሳብና በጉዳዩ ላይ እኔም እንደአንድ ዜጋ የበኩሌን ሀሳብ ለአንባብያን ለማካፈል ፈለኩ፡፡

በእኔ እምነት ጀነራሉ በዚህ ፅሁፋቸው አማራጭ የፖሊሲ ሀሳብ ማቅረብ ብቻ ሳይሆን ይህን ተከትሎ መሆንና መደረግ አለበት ብለው ያሰቡትንና ያመኑበትን ጉዳይ በትንታኔ አስደግፈው አስነብበውናል፡፡ በግሌ ከጀነራሉ ፅሁፍ ውስጥ በተለየ ሁኔታ ትኩረቴን የሳበውና ላለፉት ሁለት አስርት አመታት ውጉዝ ከመአሪዮስ ብለን በግዝት ከላያችን ጥለነው የቀየነው የጦርነት ምታ ነጋሪት እንድምታ ያለው የሚመስል አማራጭ የውጪ ግንኙነት ፖሊሲያችን አካል ልናደርግ ይገባል የሚል አቋም እያራመዱ ያሉ መስሎ የተሰማኝ በፅሁፋቸው ገፅ 9 ላይ የሰነዘሩት ሀሳብ ነው፡፡ ይህንን የጀነራሉን ሀሳብ ሳነብ አሁን ባለንበት የ21ኛው ክፍለዘመን ስልጣኔ ላይ ሆነን የ20ኛውን ክፍለዘመን አባዜ ሙሉ በሙሉ ከውስጣችን አላራገፍነውም እንዴ? ብዬ እንዳስብ አስገደደኝ፡፡

ጀነራሉ በፅሁፋቸው ፍላጎታቸውን እንዲህ ሲሉ ይነግሩናል *".....በዚህ የቀይ ባህር ቀጠና አይነተኛ ሀይል የነበረን፡፡ አሁን በዚህ መስመር ተገለን መቀመጥ አንችልም፤ አይገባንም፡፡"* ካሉን በኋላ ሀሳባቸውን በመቀጠል *".....ከዚህ ሁኔታ አንፃር በፖሊሲ ደረጃ እኛ ኢትዮጵያውያን በደቡባዊ ቀይባህር የሚደረግ ማንኛውንም እንቅስቃሴ እኛን ያገባናል የሚል ፖለቲካዊ አስተሳሰብና ከዚህ የሚመነጭ ፖሊሲ ሊኖረን ይገባል፡፡"* ብለውን ፖሊሲያችን የሌሎች አገራትን ሉአላዊነትም ማማተር እንደሚገባው ሊነግሩን ሞክረዋል፡፡ ይህንን ሀሳባቸውን በማጠናከር ቀይ ባህርን በሚመለከት ሊኖረን ይገባል የሚሉትን የፖሊሲ አማራጭ በፅሁፋቸው ገፅ 10 ላይ እንዲህ በማለት ይቋጫሉ *"ይሄ አካባቢ....."* ይላሉ ጀነራሉ *"ይሄ አካባቢ ለወደፊት ጠላቶች ሊሆኑ በሚችሉ ሀይሎች ሙሉ ቁጥጥር ስር ሆኖ*

የአገራችን ሰላም የተጠበቀ ይሆናል ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው፡፡” ብለው ከፍተኛ ስጋት ከውጪ እንደሚጠብቀን ካስጠነቀቁ በኋላ “ስለዚህ ይህ የቀይ ባህር በር የማግኘት ጉዳይና በጠቅላላው በቀይ ባህር ዋነኛ ተዋናይ መሆን ከአገር ጥቅምና ደህነት አንፃር ሲታይ እጅግ መሰረታዊ ነው” በማለት የመፍትሄ ምክራቸውን ሊለግሱን ሞክረዋል(መስመር የኔ)፡፡ እንግዲህ ጀነራሉ የይሆናልና የምናልባት ጠላትን በማሰብ ይህንን አይነት የአደጋ ትንታኔ አስቀምጠው አደጋውን ለመመከት ያስችላል ብለው ያሰቡትን የፖሊሲ አተገባበር በፅሁፋቸው ገፅ 10 ላይ “በዚህ ጉዳይ ፖለቲካዊ ስምምነት ከተደረሰና እንደ መንግስት ፖሊሲ ሆኖ ከፀደቀ ፖሊሲውን ተግባራዊ ለማደረግ የመጀመሪያው ምርጫ በሰላማዊ፤ ዴፕሎማሲያዊና በህጋዊ መንገድ ፖሊሲውን ተግባራዊ ለማድረግ መንቀሳቀስ ይሆናል፡፡” ካሉን በኋላ በዛው የፅሁፋቸው ገፅ በጉዳዩ ላይ ያላቸውን ሀሳብ ጠንከር በማድረግ “...ከዚህ አንፃር ፖሊሲውን ተግባር ላይ ለማዋል ወታደራዊ አማራጭም ከመጀመሪያው ዝግ መደረግ የለበትም፡፡” ብለውናል፡፡ በቀይ ባህር ላይ ያለንን ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ያረጋግጥልናል ብለው ያቀረቡት ሁለተኛው ወታደራዊ አማራጭ ምን አይነት ይዘት ያለው እንደሆነና በአካባቢው ያለው ፍላጎት ከመካከለኛው እስከ ሩቅ ምስራቁ፤ ከምእራብ አውሮፓው እስከ ሰሜን አሜሪካው የሚዘልቅ ሆኖ ሳለ የሳቸው ምርጫ የሆነው ወታደራዊ መፍትሄ ከማን ጋር መሆን እንደሚገባው በዝርዝር ሳያስረዱን ነገሩን በደፈናው ውስጠ ወይራ አድርገውብን አልፈውታል፡፡ ለነገሩ እኔም ሆንኩ ሌላው አንባቢ ሁለተኛ አማራጭ ብለው አውገርግረው የተዉት የሀሳብ ቋጠሮ ወታደራዊ አማራጭ መፍትሄ ከማን ጋር እንደሆነና ለዚህም መዘጋጀት እንደሚያስፈልግ እየነገሩን መሆኑን ለመረዳት የነገርን ሰምና ወርቅን የመለየት ያክል የሚከብድ አይሆንም፡፡

ይህ የጀነራሉ ሀሳብ የዝምባቡዌ ሰዎች ፈሊጣዊ አነጋገር ነው ብሎ በአንድ ወቅት ጓደኛዬ የነገረኝና እስከአሁን በትውስታዬ ተቀርፆ የቀረውን “you have little or no power over what's not yours” የሚለውን አባባል እንዳስታውስ ነው ያደረገኝ፡፡ በግሌ የሳቸውን አባባል ባልደግፍም እንደሳቸው ሀሳብ ከሆነ እንግዲህ በዚህ የአገር ደህንነት ፖሊሲ አማራጫቸው ላይ ድህነት ሲታከልበት ውጤቱ እንኳን የሌላውን የራስ ለማድረግ ይቅርና የራስንም ለማዳን ከንድ የሚያዝል መስሎ ነው የሚሰማኝ፡፡

የዚህ ፅሁፍ አቅራቢ ጀነራሉ ለምን የመሰላቸውን አማራጭ ሀሳብ አቀረቡ? በሰላማዊና ዴፕሎማሲያዊ መንገድም ይሁን በጦርነት ለምን የባህር በር ይኑረን ብለው ተከራከሩ? ለምንስ ወታደራዊ አማራጭን እንደሁለተኛ አማራጭ አድርገው አሰቡ? በሚል ሀሳባቸውን እንደ ስህተት ቆጥሮ ለመሞገት አይደለም፡፡ ይህን ማሰብ አይደለም እኔ ተራው ዜጋ ይቅርና ምንም አይነት ጉልበት ያለው ምድራዊ ሀይል ሊነጥቃቸው የማይችል ተፈጥሮአዊ መብታቸው ስለሆነ እንደ ወታደር፤ እንደ ምሁር፤ እንደግለሰብ ባለሙያ፤ እንደ ፖለቲከኛና እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በመሰላቸውና ባመኑበት መንገድ በጉዳዩ ላይ ያላቸውን ሀሳብ ሊሰነዝሩ ይችላሉ፡፡

እዚህ ላይ በግልፅ ልረዳው ያልቻልኩት ጉዳይ ለፅሁፋቸው የተለየ ርእስና የተወዛገበ አላማ አስቀምጠው በተውገረገረ መንገድ ሀሳባቸውን እንድንረዳው ከሚያደርጉን ፁሁፉን የፖሊሲ አማራጭ ሀሳብ ብለው ለምን ፊት

ለፊት አርእስት ሊሰጡት አልሞከሩም? ለምንስ በመግቢያቸው ላይ የፖሊሲ ሀሳብ ለማቅረብ አይደለም በማለት ፈራ ተባ የተሞላበት አቀራረብን መረጡ? የሚለው ጉዳይ ነው፡፡

ለአንባብያን በዚህ መልኩ የተውገረገረ ፅሁፍ ይዞ ከመቅረብ ሀሳብን በግልፅ አቅርቦ መሞገት የተሻለ ይሆን ነበር፡፡ በምንም ሆነ በምን ይምጣ በእኔ እምነት የጀነራሉ መነሻና መድረሻ የነገር ዘውግ የባህር በር ነው፡፡ ይህንንም ሰላማዊ፤ ዲፕሎማሲያዊ፤ ህጋዊ፤ ወታደራዊ አማራጭ ተጠቅመን ማግኘት አለብን ነው፡፡ ጀነራል ፃድቃን ነገራቸውን እንደዚህ የማይሸፋፈን የበሬ ግንባር አድርገው ቢቀርቡ ኖሮ ማንኛውም ሰው የመሰለውን ሀሳብ እያነሳ ሀሳባቸውን ሊደግፍ ወይም ሊሞግት ይችል ነበር፡፡ በበኩሌ ይህ የጀነራል ፃድቃን የሀሳብ ማእከላዊ እንብርትና በዚህ ዙሪያ ለማንሳት የፈለጓቸው ሀሳቦች ከአገራዊ የደህነት አስተሳሰብ እንዴት ይስማማል ወይም ይጋጫል? አሁን ካለንበት ዘመን አንፃር አስተሳሰቡ ጊዜው አልፎበታል ወይስ ተግባራዊ መሆን የሚችል ነው? የሚለውን መደምደሚያ ከንድፈሀሳባዊ ትንታኔዎች በመነሳት አንባቢ የራሱን ድምዳሜ እንዲወስድ በደህንነትና ብሄራዊ ደህነት ጉዳይ ላይ በሚነሱ ንድፈሀሳባዊ እይታዎችና ክርክሮች ዙሪያ የበኩሌን ሀሳብ እንደሚከተለው ለማቅረብ ወደድኩ፡፡

ጀነራል ፃድቃን ሊያመላክቱን እንደሞከሩት የውጪ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ የአንድ አገር ህልውናና የብሄራዊ ደህንነት ማስጠበቂያ መሳሪያ በመሆኑ ጉዳዩ ከብሄራዊ ደህንነት ተነጥሎ የሚታይ አይሆንም፡፡ በቀደሙት ጊዜያት የብሄራዊ ደህንነት አስተሳሰብ ፍልስፍናና ንድፈ ሀሳባዊ እይታ የተረጋጋ መንግስትና ሉአላዊ አገር ከመፍጠር፤ ከማጠናከርና ከመጠበቅ አስተሰሳሰብ ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ የዚህ አይነቱ የብሄራዊ ደህንነት አስተሳሰብ እያደገና እየዳበረ መሄድ የጀመረው ለአገራት ዳር ድንበር እውቅና መስጠት ካስቻለውና የሉአላዊነት አስተሳሰብ የአለም አቀፍ ግንኙነት ስርአቱ መሰረት እንዲሆን ካደረገው የአውሮፓውያኑ ሲቪል ጦርነት ማብቂያ በሆነው የዌስት ፌሊያን ስምምነት በኋላ መሆኑን በጉዳዩ ላይ የተፃፉ መዛግብት ያስረዱናል፡፡ ከዛን ጊዜ ጀምሮ በተለይ በምእራባውያኑ ዘንድ የደህንነትና የብሄራዊ ደህንነት ጉዳይ የአለም አቀፍ ግንኙነት ስርአቱ መሰረትና ምሶሶ በመሆን በርካታ አለማቀፋዊ ሂደቶችን ማለፍ ችሏል፡፡ ለመሆኑ ደህንነት፤ ብሄራዊ ደህንነትና ከዚህ ተነጥሎ ሊታይ የማይችለው ብሄራዊ ጥቅም ሲባል ምን ማለት ነው?

## ደህንነት፤ ብሄራዊ ደህንነትና ብሄራዊ ጥቅም ሲባል ምን ማለት ነው?

ጀነራል ፃድቃን በፅሁፋቸው "አላማ" ላይ ገልፀውት እንደነበረው የአገራዊ ደህንነትና የውጪ ጉዳይ ፖሊሲ ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ ታሪካዊ እድገቱን ከማስረዳት ባለፈ ብዙዎቻችንን ሊያግባባንና ጉዳዩን ከመሰረቱ ለመረዳት የሚያስችለን ጥርት ያለ ትርጉም ሳይሰጡን ያለፉ መስሎ ስለተሰማኝ ወደተነሳሁበት ነጥብ ከመግባቴ በፊት በዚህ ጉዳይ ላይ ትንሽ ልበል፡፡ እንደ ተወልደ ገብረስላሴና ዱርጋ ፕሬዝድ አገላለፅ የውጪ ግንኙነትና (ደህንነት) ፖሊሲ *"በሁኔታዎችና ውጤቶቻቸው ላይ ጥንቃቄ በተሞላው ትንተናና ትንበያ ላይ ተመስርቶ የአንድን አገር ፍላጎት የሚያንፀባርቅ፤ በአለማቀፍ ማእቀፍ ውስጥም የአገርን ብሄራዊ ጥቅም ለማስጠበቅና አገራዊ ግቦችን ለማሳካት የሚያገለግል የውጪ ግንኙነትና የብሄራዊ ደህንነት ማስፈፀሚያ ሰነድ"* እንደሆነ

ያስረዱናል፡፡(www.irjbm.org) አላማና ግቡም ሉአላዊነትንና ከውጪ የሚመጣ አደጋን መከላከል ብቻ ሳይሆን የአንድን አገር የልማት፣ ሰላም፣ መረጋጋትና የዜጎች የተሻለ ህይወት እንዲኖራቸው በማድረግ ብሄራዊ ጥቅምን ማስጠበቅና አገራዊ ግቦችን ማሳካት እንደሆነ አክለው ይገልፃሉ፡፡ ነገር ግን ጀነራል ፃድቃን የአንድን አገር የውጪ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲ ግቦች ሊያሳካ የሚችል ፖሊሲ በሚል ካስቀመጧቸው ነጥቦች ውስጥ ከጥንታዊ የደህንነት እይታ ባልተለየ *መልኩ "....ጠላት ተብለው የተለዩትን ለመነጠልና ወዳጆችን ለማሰባሰብ፣ ኢኮኖሚያዊ አቅሙንና አገራዊ ፍላጎቱን ለማሳካት ጠላቶቹንም ለማንበርከክ....ወዘተ"* በሚል ዘርዝረውልናል፡፡ ይህ አገላለፃቸው ዋነኛውን የሀገራዊ ደህንነት ስጋት ውጫዊ በማድረግ ውስጣዊ ሁኔታው ለብሄራዊ ደህንነት የሚኖረውን ጉልህ ድርሻ ችላ ያሉት አስመስሎባቸዋል፡፡ ለመነሻ እንዲሆን ይህን ያክል ካልኩ በኋላ አንባቢዎቼ እንዲረዱልኝ ወደፈለኩት መሰረታዊ ነጥብ ልመለስ፡፡

## ደህንነት ምንድነው?

ደህንነት ከጥንት ጀምሮ የሰው ልጅ ህልውናውን ለማስጠበቅ ሲያደርግ ከነበረው ትግል ጋር በቀጥታ የተያያዘና ከእድገቱ ጋር እያደገና እየጎለበተ የመጣ ክስተት ነው፡፡ በጊዜ ሂደት ከፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና የቴክኖሎጂ እድገት ጋር ማደግ የቻለው የዘመናዊ ደህንነት አስተሳሰብ ከጥንታዊ የደህንነት/security/ እይታ የተለየ ስፋትና ጥልቀት ያለው ትርጉም እየተላበሰ ቢመጣም አሁንም ደህንነት ምንድነው? የሚለው ጥያቄ አከራካሪና እንደግለሰቦች አስተሳሰብ፣ የፍልስፍ፣ የንድፈሀሳብና የፖለቲካ ርእዮት፣ የነባራዊ እውነታ አረዳድና ባህል የተለያየ ትርጉም ይሰጠዋል፡፡ በተለምዶአዊ አተረጓጎም ደህንነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከአገርና ዳር ድንበር እንዲሁም ከዜጎች ህልውና ጋር የተያያዘ ውጫዊ የሆነ አደጋ ከመኖርና አደጋውን ከመካለል ጋር የሚያያዝ ጉዳይ ብቻ ተደርጎ ስለሚታይ ደህንነት በተለያየ ሂደት የተገኙ ከፊተኛ ዋጋ ያላቸውን ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኮኖሚያዊ እሴቶችን ከአደጋ፣ ከአደጋ ስጋትና ከጥቃት መጠበቅ ብቻ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

ጀነራል ፃድቃንም በፅሁፋቸው ጠቀስ አድርገው ስለጉዳዩ ብዙ ሳያስረዱን ያለፉት ከቀዝቃዛው የአለም ጦርነት በኋላ እያደገ በመጣውና ባለንበት የ21ኛው ክፍለ ዘመን ሰፊ ተቀባይነትን ለማግኘት በቻለው በሰብአዊ ደህንነት/human security/ አስተሳሰብ መሰረት ደህንነት ከአገርና ከመንግስት የህልውና አደጋ ጋር ብቻ መያያዙ እያከተመ በመሄድ የሀገርን፣ የማህበረሰብን፣ የቡድንና የግለሰብን ህልውናና ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጣቸው እሴቶችን ለአደጋ ከሚያጋልጡ ውስጣዊም ሆነ ውጫዊ፣ ተፍጥሮአዊም ሆነ ሰውሰራሽ ስጋቶች በሙሉ መጠበቅ ተደርጎ ይታያል፡፡ አስተማማኝ ደህንነት ማረጋገጥ ሲባልም የዜጎችን፣ የማህበረሰቦችን፣ የቡድኖችን፣ የግለሰቦችን፣ የአገርንና በአጠቃላይም የአለምን ደህንነት አደጋ ላይ ሊጥሉ የሚችሉ ተጨባጭ(objective)ና የምናልባት(potential) ስጋቶችን(threats) መለየት፣ እነዚህን ለመከላከልና ለመቋቋም የሚያስችሉ መንገዶችንና ዘዴዎችን መቀየስ፣ ተገቢና ትክክለኛ መፍትሄዎችን የማፈላለግና ተግባራዊ የማድረግ ጉዳይ ተደርጎ ይታያል፡፡

በውጪ ወረራና ጥቃት ላይ ብቻ በማተኮር ወታደራዊ አቅምን እንደ ዋነኛ የደህንነት ዋስትና በመቁጠር የመንግስትንና የስርአትን ደህንነትን ማእከል ካደረገው ጥንታዊው የደህንነት አስተሳሰብ ይልቅ ሰብአዊ ደህንነትን

አዲስና የተለየ የሚያደርገው አስተሳሰቡ የኢኮኖሚ፤ የፖለቲካ፤ የምግብ፤ የጤና፤ የአካባቢ፤የግለሰብና የማህበረሰብ ደህንነትን የሚመለከቱ ዘርፈ ብዙ ገፅታዎች ያሉት በመሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ አስተሳሰብ ውስጣዊና ድንበር ተሻጋሪ ባህሪይ ያላቸው ችግሮች በሙሉ የደህንነት ስጋት እንደሆኑና ደህንነትን ማረጋገጥ ሲባልም ለነዚህ መልከ ብዙ ችግሮች የተቀናጀ ምላሽ መስጠት እንደሆነ የሚያስቀምጥ በመሆኑ ከቀደምቶቹ የደህንነት እሳቤዎች መሰረታዊ የአስተሳሰብ ሽግግር /paradigm shift/ ያስከተለ አዲስ ደህንነት አስተሳሰብ ተደርጎ ይታያል፡፡

## ብሄራዊ ደህንነት

አሁን ባለንበት ዘመን ብሄራዊ ደህንነት አንድ አገር ከፍተኛ ዋጋ የምትጣቸው እሴቶች፤ እምነቶች፤ ዴሞክራሲያዊ የአኗኗር ዘይቤዎች፤ የመንግስት ተቋማዊ የአስተዳደር ስርአቶች፤  ብልፅግና የተሞላው የዜጎችን ሰላማዊ ህይወትና የአገርን አንድነት በቀጣይነት መጠበቅና የማጠናከር ጉዳይ ተደርጎ ይታያል፡፡ ቆየት ባለው የጥንታዊ እውነታ(classical reaism) አስተሳሰብ ሉአላዊ አገርና ሉአላዊ መንግስት ሆኖ መቀጠል ብቻ የብሄራዊ ደህንነት መገለጫና መሰረት ተደርጎ መንግስት ዜጎቹን የመጠበቅና ዜጎችም መንግስት ይጠብቀኛል የሚል እምነት በመንግስት ላይ እንዲጥሉ ብቻ ይጠበቅ ነበር፡፡ ከዚህ በመነሳትም የብሄራዊ ደህንነት ትኩረቱ በአገር ዳርድንበርና በስርአት ደህነት ላይ ብቻ የታጠረ ነበር፡፡

በግሎባላይዜሽን ዘመን እየዳበረ የመጣው የብሄራዊ ደህንነት አስተሳሰብ የአገራት የደህንነት ስጋት ከተወሰነ ውጫዊ ሁኔታ ብቻ የሚመነጭ ሳይሆን ድንበር ተሻጋሪና አለማቀፋዊ ይዘት ያለው መሆኑን፤ የአገራት የደህንነት ስጋቶችም እንደ ቀድሞው ሌሎች መንግስታት ብቻ ሳይሆኑ ኮርፖሬት ድርጅቶች፤ ቡድኖች፤ ግለሰቦች ጭምር መሆናቸውንና እንደ ተደራጀ ወንጀል፤ የአካባቢ አየር ሁኔታ መበከልና መበላሸት፤ የተፈጥሮ ሀብት ሽሚያና በዚህ ምክንያት የሚፈጠር ግጭት፤ ድህንነት፤ ኋላ ቀርነትና ድርቅ የመሳሰሉ አገራዊና አለማቀፋዊ ጉዳዮች የሰው ልጆችን ደህንነት አደጋ ላይ የጣሉና ለሰውልጆች ደህንት የስጋት ምንጭ ናቸው ወደሚል አስተሳሰብ እንዲሸጋገር አድርጎታል፡፡

የዚህ የደህንነት አስተሳሰብ አቀንቃኞች በህዝቦች የሚፈጠር ችግርና አደጋ የአንድን አገር ብሄራዊ ህልውና ከማሳጣት አልፎ እንደ መንግስት ሊኖር የሚገባውን ሉአላዊ ዳርድንበር እስከማፍረስ ስለሚደርስ አገራዊ ዳርድንበር/territoriality/ እና ወታደራዊ የመከላከል ብቃት የቀድሞውን ያክል አስፈላጊነቱ ትርጉም አልባ መሆኑንና የሰው ልጆችን ሁለንተናዊ ደህንነት ለአደጋ የሚያጋልጡ ውስጣዊና ድንበር ተሻጋሪ ችግሮች እስካሉ ድረስ በወታደራዊ አቅም ብቻ አገርን ለመጠበቅና ዳርድንበርን ማስከበር ስለማይቻል ሁሉን አቀፍ የትብብር ደህነት አማራጭ የሌለው መፍትሄ ነው በሚል ይከራከራሉ፡፡

ከአለማዊ ስርአቱ መለወጥና ከላይ ከተመለከተው የደህንነት ዘርፈ ብዙ እይታ ጋር በሊበራል የፖለቲካ ዘይቤ ተግባራዊ መሆን የጀመረው የብሄራዊ ደህንነት አስተሳሰብ የብሄራዊ ደህንነት ከወታደራዊ ፉክክር፤ ሻል ሲልም ርእዮተ አለማዊ ወዳጅነት ከሚፈጥረው ትብብር አልፎ ወደ ጋራ ደህንት አስተሳሰብ/collective security/

የተሸጋገረ የርእዮተዓለም ለዘብተኝነት የሚታይበት አስተሳሰብ ነው፡፡ ይህ አስተሳሰብ ራስን ለመከላከል ካልሆነ በስተቀር ብሄራዊ ጥቅምን ለማስጠበቅ ሲባል ሀይል መጠቀም ከህግ ውጪ የሆነ ድርጊት በመሆኑ ብሄራዊ ደህንነት በትብብርና በጋራ ተጠቃሚነት ሊመሰረት ይገባል ብሎ ያምናል፡፡

በአጠቃላይ አሁን ያለንበት ዘመን የብሄራዊ ደህንነት ጉዳይ የአንድን አገር፤ መንግስትና ህዝብ የደህንነት የማረጋገጥ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የግለሰቦችን፤ የማህበረሰቦችን፤ የአገርን፤ የክፍለ አህጉርን፤ የአህጉርንና በአጠቃላይም የፕላኔታችንን የጋራ ደህንነት የማረጋገጥ ጉዳይ ተደርጎ የሚታይበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ በመሆኑም የአንድ አገር የደህንት ዋስትና የሚረጋገጠውም ሁሉንም የመንግስት አቅሞች በማጠናከርና በማመጣጠን እንደሆነና ይህ ተግባራዊ የሚደረገውም የወታደራዊ መከላከል አቅም ፍፁም ወደጎን ሳይተው ጠንካራና ለስላሳ ሀይል (hard and soft power) ተበለው የሚጠሩትን መከላለያ፤ ዲፕሎማሲና ልማት በማቀናጀት ውስጣዊ አቅምን በማጠናከርና በውጪ ግንኙነት ረገድም በጥርጣሬና በጠላትነት መፈራረጅን አስወግዶ ለጋራ ደህንነትና ተጠቃሚነት በመተባበር ብቻ እንደሆነ በጥብቅ የሚታመንበት ደረጃ ላይ ደርሰናል፡፡

**ብሄራዊ ጥቅም**

ብሄራዊ ጥቅም አገራት ከድንበራቸው አልፈው በአለም አቀፉ የፖለቲካ ስርአት ውስጥ እንዲኖራቸው ከሚፈልጉት ቦታ፤ ተጠቃሚነትና ይህንን በታ ለማግኘትና ተጠቃሚነታቸውን በላቀ ደረጃ ለማረጋገጥ መገንባት ከሚፈልጉት አቅም ጋር የሚያያዝ ጉዳይ ነው፡፡ ብሄራዊ ጥቅምና ብሄራዊ ደህንነት አንዱ ከሌላው ተነጥሎ የሚታይ ሳይሆን ሁለቱም በጥብቅ የተሳሰሩ አንደኛው ለሌላው አስፈላጊ ጉዳዮች በመሆናቸው ብሄራዊ ጥቅም የማስጠበቅ ጉዳይ ብሄራዊ ደህንነትን ከማስጠበቅ ጉዳይ ጋር ተነጥሎ የሚታይ አይሆንም፡፡ ብሄራዊ ጥቅም ሲባል የአንድን አገር ጥቅም ከውስጥና ከውጪ አደጋና ስጋት ለመከላከል የሚያስችል ዘርፈ ብዙ እይታና ምላሽ ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ ኦርቪል ኤን(1972) ብሄራዊ ጥቅሞች ለአንድ አገር ማህበረሰብ ልማትና እድገት እሴቶችና አላማዎች የሚቃኙበት አቅጣጫ ሲሆን ብሄራዊ ደህንነት እነዚህን አገራዊ እሴቶችና የልማት አላማዎች ለመጠበቅና ተፈፃሚነታቸውን ለማረጋገጥ ሲባል በጥንቃቄ የሚዘጋጅ የማስፈፀሚያ መሳሪያ ነው በሚል ብሄራዊ ጥቅምና ብሄራዊ ደህንነት ተነጣጥለው ሊታዩ የማይችሉ ጉዳዮች መሆናቸውን ለማስረዳት ይሞክራል፡፡

በሌላ በኩል ሃንስ ጄ ሞርገንቱ(1978) የተባለ ምሁር ብሄራዊ ጥቅምን በሁለት ይከፍለዋል፡፡ የመጀመሪያው ማንኛውም መንግስት ቢሆን አሳልፎ ለመስጠትና ለመደራደር ፈቃደኛ የማይሆንባቸው፤ በነዚህ ብሄራዊ ጥቅሞች ላይ አደጋ ሲያጋጥምም በጦርነት ጭምር ለማስከበር ወደኋላ የማይልባቸው የአገርን ደህንነት፤ ነፃነት፤ ሉአላዊነትና የመንግስትን ተቋማዊ እሴት የሚመለከተው ቀዳሚውና ዋነኛው የብሄራዊ ጥቅም(vital or primary national interest) በሚል የሚገልፀው ሲሆን ሁለተኛውና እንደየአገሩ ተጨባጭ ሁኔታ የሚለያይ በመሆኑ በግልፅ ለማስቀመጥ አስቸጋሪ እንደሆነ የሚገልፀው ዋነኛውን ብሄራዊ ጥቅም በላቀ ደረጃ ለማስከበር ሲባል መንግስት ሊደራደርባቸው የሚችላቸው ጥቅሞች እንደሆኑ ያስቀምጣል፡፡

የቅርቡና በአሁኑ ወቅት ገዢ የሆነው የኒዎሪያሊዝም/neorealisem/ ንድፈሀሳባዊ አስተሳሰብ አካልና ለዘብተኛ(liberalist approach) በመባል የሚታወቀው አስተሳሰብ ብሄራዊ ጥቅም በወታደራዊ ብቃትና ጥንካሬ ብቻ ሳይሆን ከዴሞክራሲና ሰብአዊ መብት መከበር፤ ከኮኖሚና የፖሊሲ ነፃነት መረጋገጥ፤ ከፍትሀዊ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት፤ ከበሽታና ድህንነት መላቀቅ ከመሳሰሉ ተጨባጭና በገሀዱ አለም ከሚታዩ ከፍተኛ ዋጋ ከሚሰጣቸው እሴቶች አንፃር መተርጎም እንደሚኖርበትና ብሄራዊ ጥቅም በዋነኝነት በውስጥ ሁኔታ ላይ ጥገኛ በመሆኑ ከውስጥ ማህበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እድገት ጋር በጥብቅ የተቆራኘ በመሆኑ በዚህ ረገድ የሚኖር የውስጥ ጥንካሬ ከውጪ የሚመጣውን አደጋ ለመከላከልና ለመመከት የሚያስችል አቅም(offencive and defensive capability) ይፈጥራል ብሎ ያምናል፡፡

## የውጪ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ መነሻዎች ምንድናቸው

ጀነራል ፃድቃን የአንድ አገር የደህንነትና የውጪ ጉዳይ ፖሊሲ መነሻዎች የአገሪቱ ህገ-መንግስት፤ አገራዊ ጥቅምና የአደጋ ትንተና እንደሆነ ገልፀውልናል፡፡ በመሰረታዊ ነጥብ ደረጃ በዚህ ጉዳይ ላይ ልዩነት ባይኖረኝም በዚህም ላይ አንዳንድ ነጥቦችን ለማለት እሞክራለሁ፡፡

ጀነራል ፃድቃን እንዳሉት ህገ-መንግስት የውጪ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲ ብቻ ሳይሆን በህገ-መንግስታዊ ስርአት ለሚተዳደር አገር ህገ-መንግስት የማንኛውም ፖሊሲም ሆነ ከዚህ የሚመነጭ ፕላን፤ ፕሮግራም ወይም ህግ መነሻ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ በእርግጥ ጀነራል ፃድቃን የግላቸው አስተያየት እንደሆነ ቢገልፁልንም *"የአገር ደህንነትና የውጪ ጉዳይ ፖሊሲ ከህገ-መንግስቱ ቀጥሎ በክብደቱና በአገር ህልውና፤ በሰላምና በተረጋጋ ሁኔታ ለማስተዳደር እጅግ መሰረታዊ ነው"* ብለውናል፡፡ ጀነራል ፃድቃን ፖሊሲው ለብሄራዊ ደህንነት ከሚኖረው ፋይዳ አንፃር በመመዘን ከህገ-መንግስት ቀጥሎ ክብደት ሰተውት ከሆነ በግሌ ብቻ ሳይሆን ፖሊሲው ውስጥም በማያሻማ መልኩ እንደተቀመጠው ለውጪ ጉዳይና ለብሄራዊ ደህንነት ፖሊሲ ተግባራዊነትና ከድህነት ባርነት አላቆ ብሄራዊ ደህንነታችን በአስተማማኝ ደረጃ ለማስጠበቅ ያስችለናል ብዬ የማምንበትና ክብደት ሲለጠው ይገባል የምለው የኢኮኖሚ ልማት ፖሊሲዎቻችን ናቸው፡፡ ምክንያቱም የህልውና፤ የደህንነትና የብሄራዊ ኩራት ዋነኛ መሰረት ኢኮኖሚ በመሆኑ፡፡

ይህንን ካልኩ በኋላ ጀነራሉ እንደጠቀሱት እንደሌሎች የአገራት ፖሊሲዎች ሁሉ የውጪ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲ መነሻ ህገ-መንግስት፤ አገራዊ ጥቅምና የስጋት ትንተና ቢሆንም እሳቸው ሊያስረዱን ካሰቡት በላይ አሁን በተግባር ላይ ያለው የውጪ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ መነሻዎቹን ልማትና ዴሞክራሲ፤ አገራዊ ክብር፤ ግሎባላይዜሽንና ግሎባላይዜሽን ውስጥ የሚያጋጥሙ ውስጣዊና ውጫዊ ፈተናዎችን ታሳቢ ያደረገ በመሆኑ ምን ያክል እጅግ ርቆ እንደሄደ ለመገመት ፖሊሲውን ማንበብ ብቻ በቂ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ ለዚህም ይመስለኛል የአገራችን የውጪ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ከተገነባበት ንድፈሀሳባዊ መሰረት፤ መርሆዎችና መነሻዎች

አንፃር ከጊዜው ጋር የሚሄድና በአንዳንድ ጉዳዮች ላይም ቀድሞ የተራመደ(move forward) ነው በሚል በበርካታ የአገር ውስጥና የውጪ ባለሙያዎች ሙገሳ ሲቸረው የምንሰማው፡፡

ጀነራል ፃድቃን ለአገራዊ ደህንነትና የውጪ ጉዳይ ፖሊሲ የስጋት ትንተና አንዱ መነሻ መሆኑን ከገለፁልን በኋላ በሳቸው ደረጃ የበሰለ የአገራዊ ስጋት ትንተና ይለግሱናል ብለን ስንጠብቅ የሰጡት አስተያየትና ስጋቱን ለመተንተን የተጠቀሙበት አገላለፅ በግሌ ከዘመኑ የደህንነት እይታ ጋር አብሮ የዘመነና ከወታደራዊ እይታ በዙ የራቀ መስሎ አልተሰማኝም፡፡ በነበሩበት የስራ ሃላፊነት ጭምር ራሳቸውም አንብበውት ይሆናል ብዬ የምገምተው Making the Twenty-First – Century Strategy: an Introduction to National Security Process and Problem በሚል ርእስ ዴኒስ ድሪው እና ዶናልድ ስኖው የተባሉ ባለሙያዎች ያስቀመጧቸውን አንዳንድ ነጥቦች እዚህ ላይ ማንሳቱ ለአንባቢ ጠቀሜታ ይኖረዋል የሚል እምነት አለኝ፡፡

እስከ ቀዝቃዛው አለም ጦርነት ማብቂያ ድረስ አለማቀፋዊ ስርአትና ዴሞክራሲ ማስፈን የሚቻለው በሀያላን አገራት(አሜሪካን)ና በጉልበት ብቻ ነው የሚለው የአክራሪ ኒዎ ሌበራሊስቶች(Neoconservatives) ራእይ ተቀይሮ አሁን ባንበት ዘመን የአለማችን አገራት የደህንነት ትንታኔ እይታና የብሄራዊ ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ(Grand Strategy) መነሻዎችን በአለማችን የተከሰቱ ሶስት ዋና ዋና ክስተቶች እንዲቀየር ያደረጉት መሆኑን ፀሀፊዎቹ ይገልፃሉ፡፡

የመጀመሪያው የቀዝቃዛው አለም ጦርነትን ማብቃት ተከትሎ የተፈጠረው አለማቀፋዊ የደህንነት ምህዳር አለማዊ የኢኮኖሚ ትስስር (Economic Globalization) የዘመኑ መገለጫ እንዲሆን በማድረጉ የሃያላኑን ፍጥጫ በማስቀረት በጠላትነት ሲፈላለጉ የነበሩ አገራት ጭምር የተሻለ አለማቀፋዊ ትብብር በመፍጠር የደህንነት ችግሮቻቸውንና ስጋቶቻቸውን ከራሳቸው አንፃር ብቻ ሳይሆን እስከ አለማቀፋዊ ገፅታው ጭምር በማየት ችግሩንም ሆነ መፍትሄውን በጋራ ለማፈላለግ እንዲገደዱ አድርጓቸዋል፡፡ የደህንነት ትብብር ባህሪይውም ከተናጠላዊ (Unilateralist) ወደ ጋርዮሽ እንዲሸጋገር (Multi-lateralist) አድርጎታል:: ይህ አስተሳሰብም አገራትን በጠላትነትና በወዳጅነት የመፈረጁ አባዜ በአብዛኛው እየቀረ እንዲሄድ በማድረግ ወደ ጋራ ትብብር እንዲሸጋገሩ አሰገድዷል፡፡ እዚህ ላይ በቀይባህር ጉዳይ ላይ ስለሚኖረን የብሄራዊ ጥቅምና የብሄራዊ ደህንነት ጉዳይ ጀነራል ፃድቃን ካነሱት ሀሳብ አንፃር አስተሳሰቡንና ከዚህ አስተሳሰብ የሚነሳውን አለማዊ እውነታ አንባቢዎቹም ሆኑ ራሳቸው ጀነራል ፃድቃን ልብ  እንዲሉልኝ ለማስታወስ እወዳለሁ፡፡

ሌላውና ሁለተኛው የአገራዊ ደህንነት ትንተና መነሻ ተደርጎ የሚታየው ወሳኝ ክስተት መስከረም 11 በኒውዮርክና በዋሽንግተን የደረሰው የሽብር ጥቃት ሲሆን እንደ ፀሀፍቱ አገላለፅ ክስተቱ በራሱ መደናገጥና ፍርሀት ከመፍጠር ባለፈ መሰረታዊ የስትራቴጂ ለውጥ ያስከተለ ባይሆንም ከቀዝቃዛው አለም ጦርነት ጀምሮ እስከ 1990ዎቹ ጊዜያት ገዢ የነበረውና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን ችላ ብሎ ለጂኦግራፊያዊ ሚሊተሪ አቅም ትኩረት ይሰጥ የነበረው አስተሳሰብ እንዲቀየር በማድረግ ለአለማቀፋዊ ሽብርተኝነት የጋራ ትግል በር የከፈተና  ወደ ጋራ የደህንነት ትብብር

እንዲሸጋገር በማድረጉ የአገራዊ ደህንነት ስጋት ትንታኔውም በዚህ አስተሳሰብ የተቃኘ እንዲሆን ማድረጉን ያስረዳሉ፡፡

እንደ ፀሀፍቱ አገላለፅ በአዲሱ የደህንነት ስጋት ትንተና አስተሳሰብ ሶስተኛውና በመሰረታዊነት የሚታየው ሌላው ጉዳይ የአገራት ደህንነት ስጋት አይነቶች በስፋትና በይዘታቸው እጅግ የገዘፉ መሆንና ስጋቶቹ የአንድ አገር ችግርና በዛ አገር ውስጥ ብቻ ተወስነው የሚቀሩ ሳይሆን በርካታ አገራትን የሚነኩና አለማቀፋዊ ባህሪይ እየተላበሱ የመጡ መሆኑ ነው፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች መኖር የደህንነት ስጋት ትንተናዎችና የፖሊሲ ቀረፃ ስራዎች በተወሰኑ አካላት ሳይሆን እንደአስፈላጊነቱ አለማቀፋዊ ተሳትፎና ድጋፍ ጭምር የሚጠይቅ እንዲሆን ማድረጋቸውን ፀሀፍቱ ያስረዳሉ፡፡ በመሆኑም የአገራዊ ደህንነት ስጋት ትንተና በዋነኝነት መነሻ ማድረግ የመገባው አገራዊ ህልውናን በመፈታተን ለመበታተን አደጋ ሊያጋልጥ በሚችል ውስጣዊ ችግር ላይ የማጠንጠኑ ተገቢነት የሚያከራክር ጉዳይ አይሆንም፡፡ ከዚህ አንፃርም የአገራችን የውጪ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲ ዋነኛው ጠላት ከውጪ የሚመጣብን ሳይሆን በውስጣችን ለዘመናት አብሮን የኖረው ድህነትና ኋላ ቀርነት መሆኑን በማስቀመጥ ከዚህ የብሄራዊ ህልናችን አደጋ ፈጥነን ለመላቀቅና ብሄራዊ ደህንነታችንን በአስተማማኝ መሰረት ላይ ለመገንባት  ፈጣን የኢኮኖሚ ልማትን፤ ዴሞክራሲንና ሰላምን የፖሊሲው ማጠንጠኛ ማድረጉ ለክርክር መቅረብ ያለበት ጉዳይ መስሎ አይሰማኝም፡፡ ከዚህ የሚመነጭ የውጪ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲ በጉልበትና ወታደራዊ አቅም ላይ የሚመሰረት ሳይሆን ከማንኛውም አገር ጋር በጋራ ትብብርና ተጠቃሚነት ላይ የተመሰረተና የጋራ ስጋትን በመከላከል ላይ ያተኮረ ትብብር መፍጠር የሚያስችል ሁኔታ እንደሚፈጥር በቀላሉ መረዳት ይቻላል፡፡

### የብሄራዊ ደህንነትና የውጪ ጉዳይ ፖሊሲ እንዴትና በማን ይቀረፃል?

ጀነራል ፃድቃን የውጪ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲ እንዴትና በማን ይቀረፃል? ለሚሉ በጭንቅላታችን ቀድመው ለሚመላለሱ ጥያቄዎች የማያደናግሩ መልሶች ሳይሰጡን ማለፋቸው ሳይበቃ የውጪ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲው በተወሰኑና በአንድ ወቅት በስልጣን ላይ የነበሩ ጥቂት የመንግስት ሀላፊዎች ፍላጎት መገለጫና የአንድ ፓርቲ የፖሊሲ ምርጫ እንደሆነ፤ ፖሊሲው የተቀረፀበትና ተግባር ላይ ስለዋለበት ሂደትም ብዙዎቻችን ከምናውቀው እውነታ የተለየና የህዝብ ተሳትፎ የተነፈገው እንደሆነ አድርገው ሊያስረዱን ሞክረዋል፡፡ የአገራችንን የውጪ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ቀረፃ ሂደት እንዲሁም በሂደቱ የነበሩ እውነታዎችን ከማንሳቴ በፊት በሚገባ ሳያስረዱን ያለፉትንና በበርካታ ዴሞክራቲክ አገራት የተለመዱ የውጪ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ቀረፃ ሂደቶች ማስረዳቱ የሚጠቅም መስሎ ስለተሰማኝ ለአንባብያን ግንዛቤ የተወሰኑ ነጥቦችን ላነሳ ወደድኩ፡፡

አሁን ባለንበት የብሄራዊ ደህንነት አስተሳሰብ የአንድ አገር የደህንነትና ውጪ ጉዳይ ፖሊሲ ቀረፃና ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት አገሪቷ ከምትከተለው ርእዮተአለማዊ አስተሳሰብ፤ ከምትገኝበት ውስጣዊ ሁኔታ፤ ወደፊት ልትደርስበት ከምትፈልገው አገራዊ ራእይ እንዲሁም ከአካባቢያዊ፤ አህጉራዊና አለማቀፋዊ ነባራዊ እውነታ የሚመነጭ ነው፡፡ በመሆኑም ከዚህ የውጪ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲ መርህና መሰረታዊ ምሶሶ የሚነሳ የውጪ ጉዳይና ደህንነት

ፖሊሲና ስትራቴጂ ቀረፃ አገራዊ ላማዎችን በማስፈፀም ብሄራዊ ደህነትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ መንገዶችንና ዘዴዎችን በሚገባ የመምረጥና ተግባራዊ የማድረግ የአመራር ጥበብ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

በብሄራዊ ደህንነትና የውጪ ጉዳይ ፖሊሲና ስትራቴጂ ቀረፃ ላይ ሁሉም አገራት አንድ አይነት የሆነ ዘዴና መንገዶችን አይጠቀሙም፡፡ አንዳንድ ሰዎች የፖሊሲና ስትራቴጂ ቀረፃው በርካታ ባለሙያዎችን የሚያካትትና በርካታ ተቋማት የሚሳተፉበት ተግባር (Multi-Disciplinary and Multi-Agency Exercise) ነው ብለው ይከራከራሉ፡፡ ይህንን አስተሳሰብ መሰረት በማድረግም ብዙውን ጊዜ የፖሊሲና ስትራቴጂ ቀረፃ ጉዳይ በአንድ ወይም በተወሰኑ የመንግስት ተቋማት ብቻ የሚከናወን ሳይሆን ውስጣዊና ውጫዊ የአገራዊ ደህንነት ስጋቶችን በመከላከልና በመመከት ረገድ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ሚናው ያላቸው ዲፓርትመንቶች(የመንግስት ተቋማት) በሙሉ በየደረጃው ተሳትፎ የሚያደርጉበት ሂደት እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ ነገር ግን በበርካታ አገራት ሁሉንም ዲፓርትመንቶች በደህንነትና ፖሊሲ ቀረፃ ስራዎች በዝርዝርና በእኩል ደረጃ ማሳተፍ የሚኖረውን አደጋ ግምት ውስጥ በማስገባት እያንዳንዱ ዲፓርትመንትና ኤጀንሲ ስለብሄራዊ ደህንነትና የውጪ ጉዳይ ፖሊሲ በሚያውቀው፤ በሚመለከተውና በተለየ ትኩረት ልክ ደረጃ በደረጃ እየወረደ(watered dowen) ግብአት እንዲሰጥ ያደርጋሉ፡፡ በመጨረሻም ከሚመለከተው የመንግስት አካል ጋር በመቀናጀት የመጨረሻ የብሄራዊ ደህንነትና የውጪ ጉዳይ ፖሊሲውን ቀረፃ የሚያከናውኑት ወይም መልክ የሚያስይዙት ግለሰብ ባለሙያዎች ይሆኑና እንደየአገሩ ሁኔታ በህግ አውጪው አካል ፀድቆ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ የቁጥጥርና የክትትል ስርአቱ እንደየአገሩ ሁኔታ የሚለያይና ወጥ የሆነ አሰራር ባይኖረውም ዋነኛ ባለቤቱ ግን የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ወይም ፓርላማው ይሆናል፡፡ እንደዚህ አይነቱ አሰራር በሰለጡና ዴሞክራቲክ በሚባሉ አብዛኞ አገራት ተግባራዊ የሚደረግ ተመራጭና ዴሞክራቲክ የሆነ አሰራር ነው፡፡

የአገራችን የውጪ ጉዳይና የደህነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ቀረፃም ከዚህ በተለየ መንገድ ጀነራሉ እንዳሉት በጥቂት የመንግስትና የፓርቲ ሃላፊዎች የወጣና የአንድ ፓርቲ ፍላጎት የተንፀባረቀበት ሳይሆን የፖሊሲው መነሻ በሆነውና እሳቸውም የፖሊሲ መነሻ ብለው ባስቀመጡት በህገ-መንግስቱ አንቀፅ 86 ከንኡስ አንቀፅ 1-6 በተዘረዘሩት የውጪ ግንኙነት መርሆዎችን መሰረት የተዘጋጀና በአብዛኞቹ ዴሞክራሲያዊ ሀገራት እንደሚደረገው በረቂቁ ላይ ይመለከታቸዋል የሚባሉ ባለድርሻ አካላት ተሳትፈውበት፤ ሀሳባቸውን ሰጥተውና ተከራክረውበት፤ ተጨማሪ ግብአቶችን አክለው ካዳበሩት በኋላ በድረ-ገፆች ላይ ሳይቀር ይፋ ተደርጎ ሁሉም ወገን እንዲያውቀውና እንዲተችበት ተደርጎ እንዲፀድቅ የተደረገ ነው፡፡ የፖሊሲው ፈፃሚና አስፈፃሚ አካላትም በፖሊሲው አፈፃፀም በሚኖራቸው የስራ ድርሻ ልክ ስለአፈፃፀሙ ለፓርላማው ሪፖርት ያቀርባሉ፤ ፓርላማውም ግልፅ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ አፈፃፀሙን እንደሚከታተል እኔም ሆንኩ እርሶ በሚዲያ የምንከታተለው ጉዳይ በመሆኑ ብዙ የሚያከራክር አይመስለኝም፡፡ እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ ፖሊሲው የህዝብ ተሳትፎና አስተያየት የተነፈገው እንደሆነ ለማቅረብ የሞከሩበት መንገድ ግን ፍፁም የተሳሳተ መሆኑን አንባቢዎቼ እንዲረዱልኝ እፈልጋለሁ፡፡

**የማን ደህንነት ነው የሚጠበቀው?**

ጀነራሉ የማን ደህንነት ነው የሚጠበቀው? ደህንነቱስ በምን ያክል ዋጋ ነው መጠበቅ ያለበት? በሚለው ጉዳይ ላይም ባለሙያዎቹ ጥንታዊ የደህንነት አስተሳሰብ ብለው በሚጠሩት መንገድ ነው ሊያስረዱን የሞከሩት፡፡ በጀነራሉ አገላለፅ የደህነት ተጠባቂ አካላት ከፖሊሲው የሚመነጭ የአንድ ወይም የሁለት ተቋማት መደበኛ የደህንነት ጥበቃ ስራ የሆነውን የወሳኝ ተቋማት ጥበቃ /Critical Infrastructure Protection/ ስራ አድርጌ ስለምገምተው ስለ ወንዞቻችን፤ የኤሌክትሪክ ማመንጫ ግድቦቻችን፤ የባቡርና ዋና ዋና የትራንስፖርት አውታሮቻችን ወዘተ... በማለት ሊያመላክቱን ሞክረዋል፡፡ ይህ እይታቸው ከፖሊሲ አንፃር ሲታይ እጅግ የጠበበ ከመሆኑም በላይ በአሁኑ ዘመን የደህንነት ተጠባቂ አካላት/referent object/ የሚባሉ መሰረታዊ ጉዳዮችን ፍፁም የዘነጉት መሆኑን ያመለከተታል፡፡

አሁን ባለንበት ዘመን ዋነኛ ተጠባቂ አካላት ጀነራሉ የጠቀሷቸው መሰረታዊ የአገራዊ እሴቶች ባለቤትና ተጠቃሚ የሆኑ ዜጎች፤ ቡድኖችና ማህበረሰቦች መሆናቸውን ላስታውሳቸው እፈልጋለሁ፡፡ የአንድ አገር ዜጎች ደህንነት ካልተጠበቀና ዜጎችን ለአደጋ የሚያጋልጡ ሁኔታዎች ባሉበት ሁኔታ ዋጋ የሚሰጣቸው እሴቶች ትርጉም አልባ ይሆናሉ፡፡ ይህንን ለማለት ያስገደደኝን ምክንያት ከንድፈሀሳባዊ መሰረቱ አንፃር አንባቢዎችም ሆኑ ራሳቸው ጀነራሉ ሁኔታውን በትክክለኛው መነፅር ለመገምገም እንዲያስችላቸው የማን ደህንነት ነው የሚጠበቀው? በሚለው ጉዳይ ላይ ቀደም ባሉት ዘመናትና በአሁኑ ወቅት ገዢ ከሆነው ንድፈሀሳባዊ አስተሳሰብ የተወሰኑ ነጥቦችን በአጭሩ ላንሳ፡፡

የማን ደህንነት ነው የሚጠበቀው? በሚለው ጥያቄ ላይ ጥንታዊ እውነታ(classical realism) በመባል በሚታወቀው የቆየው ደህንነት አስተሳሰብና ኒዎሪያሊዝም(neorealisem) እየተባለ በሚጠራውና ሰፊ ተቀባይነትን በማግኘት እያደገ ከመጣው የዘመናችን የሰብአዊ ደህንነት አስተሳሰብ መካከል ሰፊ የሆኑ ልዩነቶች ይታያሉ፡፡ በጥንታዊው የደህንነት አስተሳሰብ የደህነት ዋነኛ ተጠባቂ አካል (referent object) አገርና ስርአት ወይም መንግስትና ተቋማዊ መዋቅሩ ብቻ የነበረ ሲሆን ከዚህ የተለየው ለደህንነት ጥልቀትና ስፋተ ያለው ትርጉም በመስጠት የደህንነት ተጠባቂ አካላት(referent objects) ሰፊ መሆናቸውን የሚከራከረው የ21ኛው ክፍለዘመን የሰብአዊ ደህንነት አስተሳሰብ እንደቀድሞዎቹ የደህንነት አስተሳሰቦች  የደህንነት ተጠባቂ አካላት(referent objects) አገር መንግስትና  ስርአት ላይ ብቻ የታጠረ ሳይሆን አገርንና የአገር ተቋማዊ እሴቶችን ጨምሮ ማህበረሰባዊ ቡድኖችን፤ ግለሰቦችን፤ አካባቢን በአጠቃላይም ለሰው ልጆች ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጣቸው ቁሳዊና ቁሳዊ ያልሆኑ እሴቶችን መሆን አለበት በሚል ያምናል፡፡ ይህ በመሆኑም አሁን ባለንበት ዘመን የደህንነት ተጠባቂ አካላት ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጣቸው እሴቶች/Cherished Values/ ብቻ ሳይሆኑ ግለሰቦች፤ ቡድኖች ማህበረሰቦችና ቁሳዊና ቁሳዊ ያልሆኑ እሴቶቻቸውና ፍላጎታቸው ጭምር መሆናቸው ልብ ሊባል ይገባል፡፡

**ብሄራዊ ደህንነት እንዴት ይረጋገጣል?**

ብሄራዊ ጥቅም ከብሄራዊ ደህንነት ተለይቶ እንደማይታይ ሁሉ ብሄራዊ ደህንነትን የማረጋገጥ ጉዳይ በቀጥታ ብሄራዊ ጥቅምን ከማስከበርና ከማስጠበቅ ጋር ተነጥሎ የሚታይ አይሆንም፡፡ ከላይ በአጭሩ ለማመላከት እንደተሞከረው በጥንታዊ የእውነታ(classical realisem) አሰተሳሰብ ብሄራዊ ጥቅምን በማስከበር ብሄራዊ ደህንነትን ማረጋገጥ የሚቻለው የወታደራዊና ዲፕሎማሲ አቅምን በማሳደግ የሀይል ተወዳዳሪነትን መፍጠር ሲቻል እንደሆነ ይታመናል፡፡

አሁን በምንገኝበት የዘመነ ግሎባላይዜሽን ብሄራዊ ጥቅምን በማስጠበቅ ብሄራዊ ደህንነትን ማረጋገጥ የሚቻለው በሀገር ውስጥ የሚገኙ የኢኮኖሚ እድገትና የፖሊሲ ነፃነትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ሁሉን አቅሞችን አሟጦ በመጠቀም የተወዳዳሪነት፤ የተደራዳሪነትና የተፅእኖ ፈጣሪነት አቅምን መጨመር ሲቻል ነው፡፡ ይህ እውን ሊሆን የሚችለው የብሄራዊ ደህንነት አደጋ ዋነኛ ምንጭና መነሻ ውስጣዊ እንደሆነ አሁንም በጥብቅ በማመን እነዚህን ችግሮች ለመፍታት እረፍት የለሽ ጥረት ሲደረግ ብቻ ነው ብሄራዊ ጥቅማችንን በማረጋገጥ የደህንነታችን ዋስትና በጠንካራ መሰረት ላይ ሊገነባ የሚችለው፡፡ በህገ-መንግስታችንም ሆነ በፖሊሲው እንደተቀመጠው የብሄራዊ ደህንነታችን መሰረትና ምሶሶ ሰላም፤ ዴሞክራሲና ልማት በመሆናቸው በየትኛውም መመዘኛ ይህ ለምን ሆነ ብሎ የሚከራከር ወገን ይኖራል ብዬ የምገምተው ጉዳይ አይሆንም፡፡ የፖሊሲው ሁለንተናዊ ቅኝት ከነባራዊ እውነታው የሚነሳና ማጠንጠኛው ሰላም፤ ልማትና ዴሞክራሲ በመሆኑ የትኛውም አይነት ስርአት ቢቀየር ከዚህ መሰረታዊ መርሆ መውጣት የሚያስችለው ሁኔታ ሊኖር አይችልም፡፡ ጀነራሉ እንደጠቆሙትም ፖሊሲውን ማሻሻል እንኳን ቢያስፈልግ መሰረታዊ የፖሊሲው መርሆዎችና የተገነባባቸው መሰረቶች ለድርድር የሚቀርቡ መስሎ አይሰማኝም፡፡ የእነዚህ መሰረታዊ መርሆዎች እውን መሆን ለኢኮኖሚ እድገትና ማህበራዊ ፍትህ መሰረት ስለሚሆኑ የዜጎችን የተላደለ ኑሮ፤ እድገትና ዴሞክራሲያዊ እሴቶች ማረጋገጥና ማጎልበት ያስችላሉ፡፡ ይህ በበኩሉ የተፋጠነ የኢኮኖሚ እድገትን እንዲሁም በአለም አቀፉ መድረክ የኢኮኖሚና የገበያ የተወዳዳሪነት አቅምን ማጎልበት ስለሚያስችል የኢኮኖሚ ነፃነትን፤ የተወዳዳሪነትና የተደራዳሪነት አቅምን በማሳደግና በማረጋገጥ በጦርነት ከመፈላለግ ይልቅ በጋራ ተጠቃሚነት የማመን ብቃት ይፈጥራል፡፡ ከዚህ አልፎ የውስጥ ጥንካሬያችን በሀይል ሊመጣ የሚችል የውጪ አደጋን ከመከላከል ባሻገር ስጋቱና አደጋው በሚጠይቀው ልክ ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት ያግዛል፡፡ ከዚህ አንፃር ጀነራል ፃድቃን የአንድ አገር የደህንነትና የውጪ ጉዳይ ፖሊሲ ሊያሳካ ይገባቸዋል ብለው ያስቀሟቸው ግቦች ከላይ ከተመለከቱት የጥንታዊ እውነታ የደህነት አስተሳሰብ ቅኝት ማአቀፍ ውጪ ሆነው የሚታዩ አይደሉም፡፡

በአዲሱ የብሄራዊ ደህንነት አስተሳሰብ የደህንነት ግቦች ሁለንተናዊ ቅኝት የብሄራዊ ደህንነት አደጋ ስጋቶች ውስጣዊ ከሆነ የአደጋ ተጋላጭነት የሚመነጩ በመሆኑ ብሄራዊ ደህንነትን ማረጋገጥ የሚቻለው ለውስጣዊ አደጋ ተጋላጭነት ለሚዳርጉ የስጋት ምንጮች ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ሁለንተናዊ አቅም መፍጠር ሲቻል ብቻ መሆኑን ያሰምርበታል፡፡ ከዚህ አንፃር ነው የውጪ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲያችንም ሆነ የሌሎች አገራዊ

ፖሊሲዎቻችን ሰላም፤ ልማትና ዴሞክራሲን የሁሉ ነገራቸው ማጠንጠኛ ያደረጉት፡፡ እዚህ ላይ የሚመለከታቸው የመንግስት አካላትም ልብ ብለው ሊያስቡበትና እንደሌሎቹ የፀረ-ድህነት ትግሎች ሁሉ እንቅልፍ አጥተው ሊሰሩበት የሚገባ መስሎ የሚሰማኝን አንድ መሰረታዊ ነጥብ አንስቼ ፀሁፌን ልቋጭ፡፡ በሌተና ጀነራል ፃድቃን ደረጃ ለብሄራዊ ደህንነት አደጋ ተጋላጭ የሚያደርገና ሲከፋም ራሳችንን መከላከል ይቅርና እንደሀገር ሊበታትነን የሚችለውን ድህነት፤ ኋላ ቀርነትና ከነዚህ የሚመነጩትን ሙስናና የመልካም አስተዳደር እጦት የመሳሰሉ መሰረታዊ የብሄራዊ ደህንነት አደጋዎችን ወደጎን በመተው ዋነኛ አደጋውን ውጫዊ አድርገው በጉዳዩ ላይ ከተከራከሩ፤ በእርግጥም መንግስት የብሄራዊ ደህንነታችን አደጋ ምንጭ ምን እንደሆነና ከምን እንደሚነሳ በጉዳዩ ላይ በህዝቡ ዘንድ የጋራ መግባባት ለመፍጠር እዚህ ግባ የሚባል ስራ ያልሰራ መሆኑን መገመት አይከብድም፡፡ በመሆኑም ከውጪ ይቃጣብናል ብለን ለምናስበው ማንኛውም አደጋ ሊኖረን የሚገባ ቀድሞ የመከላከል ዝግጁነት እንደተጠበቀ ሆኖ (ይህም በአስተማማኝ የሚረጋገጠው ኢኮኖሚያችን ሲያድግ ብቻ እንደሆነ ልብ ይሏል) በዋነኛው የብሄራዊ ደህንነታችን አደጋ ምንጭ ላይ በህዝቡ አንድ አይነት ብሄራዊ መግባባት ለመፍጠር የሚያስችል ሰፊ ስራ በተከታታይ ካልተሰራ ከዋናው የፀረ-ድህነት፤ የመልካም አስተዳደርና የፀረ-ሙስና ትግል አጀንዳችን የሚነቅለን መስሎ ነው የተሰማኝ፡፡ ይህ እንዳይሆን ልብ ያለው ልብ ይበል ብቻ ሳይሆን ከልቡ ይትጋ እላለሁ፡፡